# ፖሊሲ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ
BOARD OF EDUCATION OF MONTGOMERY COUNTY

---

ተዛማጅ ደንቦች፦ **ACA,** BBB, GBA, ~~GBA-RA, GBH, GBH~~**GBB**-RA, GCA-RA, **GCB, GJA-RA, GMD-RA, GMG-RA, GKA-RA,** HDA, HDB, HDC

ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦ ~~የሰው ሀብት~~የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

## የሥራ ግብረኃይል ልህቀት የስራ ኃላፊነት

## ~~ራዕዩን በሚያደርስ ድርጅት ውስጥ ያለ አዎንታዊ የስራ አካባቢ/ድባብ~~

~~6.A.~~ ዓላማ

ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ግብረኃይል ልህቀት እና ድርጅታዊ ጥንካሬ ምላሽ ሰጪ፣ ስልታዊ፣ እና ቀጣይነት ያለው የሰራተኞች የሙያ እድገት ሂደቶች ላይ የተመሰረቱ መሰረታዊ መዋቅሮችን እንደሚከተለው ለማቋቋም፦

1. አዳዲስ ሰራተኞችን ከድርጅቱ ጋር ማስተዋወቅ፣ ስልጠና መስጠት፣ እና ሰራተኞች የተመደቡበትን ስራቸውን እንዲሰሩ እና ባሉበት የስራ መደባቸው ላይ ለሚኖሩ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ምላሽ መስጠት መቻላቸውን መገምገም፣

2. የሰራተኞችን የሙያ ትምህርት ፍላጎቶች ማጎልበት እና ሰራተኞች አዳዲስ ብቃቶችን እንዲያዳብሩ እና በእቅድ እና ለሙያ እድገት በሚያዘጋጃቸው ሙያዊ ትምህርት የአመራር ዕድሎች ፍላጎት እንዲኖራቸው ማበረታታት፣ እና

3. የግለሰቦች የስራ አፈፃፀም የሚጠበቅባቸውን ብቃት እና ደረጃዎችን ሳያሟላ ሲቀር የተዋቀረ፣ ወቅታዊ እና ውጤታማ ምላሽ እና እርማት መስጠት።

~~የትምህርት ቦርድ የመማር፣የማስተማር፣ እና የአስተዳደር ሂደቶችን በማሻሻል ረገድ ሙያዊ እድገትን እና የሰራተኛ ስኬትን ለመደገፍ ለሁሉም ሰራተኞች የሙያ እድገት ስርዓቶችን ለመዘርጋት፣ ስለ ትብብር፣ በከፍተኛ ደረጃ ስለሚጠበቁ የሥራ ኃላፊነቶች፣ እና በአካባቢ፣ በስቴት፣ እና በፌደራል ህግ መሰረት አድሎአዊ ባልሆነ መልኩ እርስ በእርስ መከባበር የሠፈነበት አካባቢ/ድባብ እንዲኖርበት ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።~~

~~7.B.~~ አቋም

1. የቦርዱ ዋና ዓላማ ሁሉም ተማሪዎች በእውቀት እንዲበለጽጉ ማዘጋጀት መሆኑን ያረጋግጣል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዋና ዓላማውን የማሳካት ችሎታ መሰረቱ ሰራተኞቹ ናቸው – ሰራተኞች በየቀኑ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ተማሪዎችን ለመማር እና በእውቀት ለመበልጸግ ያዘጋጃቸዋል፤ ለተማሪዎች፣ ለ MCPS ማህበረሰብ ትምህርት፣ ደህንነት፣ እና ስኬት አስተዋፅዖ ያደርጋል።

    a) የቦርዱ ጥብቅና ጠንካራ የመከባበር ባህል ሁሉም ሰራተኞች እና ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ከፍተኛ የአፈጻጸም ደረጃዎችን እንዲተገብሩ አስተዋፅዖ አድራጊዎች መሆናቸውን በመገንዘብ ለሁሉም ሰራተኞች ሚና እውቅና ይሰጣል።

    b) በ MCPS ውስጥ በሁሉም የስራ መደቦች ላይ የሚገኙ ሰራተኞች፣ ከተማሪዎች ጋር ያላቸው ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ የዕለት ተዕለት ግንኙነት፣ የስራ ልምድ፣ አንድ የሚያደርጓቸው ጉዳዮች ወይም ልዩነቶቻቸው ምንም ይሁን ምን፣ ሁሉም ተማሪዎች በእውቀታቸው እንዲበለጽጉ የማዘጋጀት የጋራ ተልዕኮ እንዳላቸው ይጋራሉ፤ እና ይህንኑ ተልዕኮ ለማስፈፀም አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

    c) ቦርዱ ለህዝብ ትምህርት የላቀ አገልግሎት ላበረከተ/ች ሰራተኛ ወይም ሁሉም ተማሪዎች በእውቀታቸው እንዲበለጽጉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚያዘጋጁ ግለሰብ ሰራተኞች ወይም የሰራተኞች ቡድን በ MCPS ለሚያደርጉት የላቀ አስተዋጽዖ እውቅና ይሰጣል።

2. ቦርዱ ለ MCPS ድርጅታዊ ጥንካሬ መሰረት ለሆኑት ለ MCPS ሰራተኞች ያለውን ቁርጠኝነት ያረጋግጣል።

    a) የሰራተኛ ብቃት ሲጨምር እና የመሪነት አቅም እንዲጎለብት ሲደረግ ግለሰቦች እና MCPS በአጠቃላይ ለማያውቋቸው/ለአዳዲስ ወይም ፈታኝ ለሆኑ ሁኔታዎች በብቃት እና ፈጠራ በተሞላበት መልኩ ምላሽ መስጠት፣ በጽናት መቋቋም እና ተባብረው መስራት ይችላሉ።

    b) ቦርዱ ሁሉንም ተማሪዎች ለመደገፍ የሁሉንም ሰራተኞቻችንን የተለያዩ እውቀቶችን እና ልምዶችን የሚያሳትፍ እና የሚጠቀም በሙያ የበለፀገ ማህበረሰብን ለመገንባት ይፈልጋል።

3. MCPS ሰራተኞቹን በፍትሃዊነት እና በአክብሮት በመገምገም ለፍትሃዊነት እና አድልዎ የሌለበት አሠራር በመዘርጋት ረገድ ቀጣይነት ያለው ቁርጠኝነቱን ይተገብራል። ቦርዱ በሁሉም የሰራተኛ ማህበራት ውስጥ ላሉ ሰራተኞች የሙያዊ እድገት ስርዓቶችን ማሳደግ ላይ እውቅና ከተሰጣቸው የሰራተኞች ቡድን ጋር በትብብር ይሰራል ይህም ቢያንስ ዋና ዋና ብቃቶችን፣ የአፈጻጸም ደረጃዎችን፣እና የግምገማ እና የግብረ መልስ የጊዜ ሰሌዳዎችን እና መስፈርቶችን/መመዘኛዎችን ያካትታል።

C. የአተገባበር ስልቶች

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስልቶችን ማዘጋጀት እና በዚህ ፖሊሲ መርሆዎች በመመራት የሙያ እድገት ስርዓቶችን በስርዓት-አቀፍ ደረጃ ለመተግበር ሀላፊነቶችን መስጠት አለበት።

1. በከፍተኛ ~~ደረጃ~~ የሚጠበቁ *የሥራ ውጤቶችን* ለመደንገግ እና ሰራተኞች በሚሰሯቸው ስራዎች ላይ ቅልጥፍና እና ብቃትን ለማሳካት ወቅታዊ እና ውጤታማ ለሆነ ሙያዊ እድገት፣ ድጋፍ፣ እና ግምገማ በሁሉም የ MCPS ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ውስጥ ባሉ መሪዎች ዘንድ የጋራ ሃላፊነት ሊኖር ይገባል። ይህም እንደሚከተለው ይተገበራል፦

a) በ MCPS ውስጥ በአዳዲስ የስራ መደቦች ላይ የተቀጠሩ አዳዲስ ሰራተኞችን ከድርጅቱ ጋር ማስተዋወቅ እና ስልጠና መስጠት።

b) ለሰራተኞች በዕለት ተዕለት የሚሰጥ ድጋፍን እና ቀጣይነት ያለው ግብረመልስን የሚያካትት በመማር ልምድ ላይ ያተኮረ ክትትል ማድረግ።

c) ለህዝብ ትምህርት የላቀ አገልግሎት ላበረከተ/ች ሰራተኛ ወይም ሁሉም ተማሪዎች በእውቀታቸው እንዲበለጽጉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚያዘጋጁ ግለሰብ ሰራተኞች ወይም የሰራተኞች ቡድን አማካይነት ለ MCPS ለተደረጉ የላቀ አስተዋጽዖዎች እውቅና መስጠት።

d) ሰራተኞችን መገምገም እና ለእያንዳንዳቸው የስራ መደቦች ከተቀመጡ የጊዜ ሰሌዳዎች እና አስፈላጊ ከሆኑ ዋና ዋና ብቃቶች እና የአፈጻጸም ደረጃዎች ጋር የሚጣጣም ተግባራዊ ግብረመልስን በወቅቱ መስጠት።

e) ወደፊት ጥቅም ላይ ሊውሉ ስለሚችሉ መገልገያዎች/ሪሶርሶች እና በግምገማ ሂደቶች ውስጥ በተዘዋዋሪ የሚፈጸሙ ማንኛውም አካሄዶች/አድሎአዊ አሰራሮች ላይ ግንዛቤን ለማሳደግ እና የዚህ ዓይነቱ ምግባር MCPS ውስጥ እንዳይቀጥል ለማድረግ ሁሉን አቀፍ፣ ባህልን ባከበረ መልኩ ምላሽ ሰጪ የሆነ ሙያዊ ትምህርት መስጠት እና ተግባራዊ ማድረግ።

2. በሁሉም የ MCPS ደረጃዎች ያሉ ሰራተኞች ሙያዊ ፍላጎቶቻቸው እንዲያድግ፣ አዳዲስ ብቃቶችን እንዲያዳብሩ፣ እና ወደ ስራ እድገት የሚያመሩ የአመራር እድሎች ፍላጎት እንዲኖራቸው ማበረታታት። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚከተሉትን ለማከናወን የአሰራር ሂደቶችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል –

a) ለሁሉም ሰራተኞች ሙያዊ ፍላጎታቸውን እንዲያሳድጉ፣ አዳዲስ ብቃቶችን የማዳበር እና ቀጣይነት ባለው ሙያዊ ትምህርት አማካይነት የአመራር ዕድሎችን የመፈለግ እድሎችን ለመስጠት የወደፊቱን በማሰብ አዳዲስ አሰራሮችን እና ፈጠራዎችን ማዳበር፤

b) እነዚህን እቅዶች ከገንዘብ አንጻር በሚቻል መልኩ እና ለ MCPS ተልዕኮ እና ስቴት ማረጋገጫ መስፈርቶች ተገቢ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ መገልገያዎችን/ሪሶርሶችን ማቅረብ፤

c) ተመሳሳይ በሆኑ የሀላፊነት ዘርፎች ውስጥ የሙያዊ ትምህርት ማህበረሰቦችን ለማበረታታት፣ እና አግባብ በሆነ መልኩ እና በተቻለ መጠን ለተለያዩ የስራ መደቦች ሰራተኞችን ለመመደብ ከሰው ሀብት እና ልማት ጽ/ቤት/Office of Human Resources and Development ውጪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች የተፈጠሩ የትምህርት እድሎችን ማስተባበር፤ እና

d) ሰራተኞችን በሥራ ላይ የማቆየት እና ከድርጅት የሚወጡበትና የሚተኩበት መረጃን እንዲሁም ሌሎች የድርጅት ፍላጎቶችን መሰረት በማድረግ ለመተካት አስቸጋሪ የሆኑ የስራ መደቦችን መለየት፣ እና ለእነዚህ ክፍት የስራ መደቦች የሚያመለክቱ የአመልካቾችን ቁጥር ለማሳደግ ስልጠና እና የክህሎት ማዳበሪያ ለመስጠት በህግ በሚፈቀደው መሠረት የታለሙ/ዒላማ የተደረጉ እቅዶችን ማዘጋጀት።

3. በዝርዝር የተቀመጡ መሰረታዊ ብቃቶችን ወይም የአፈጻጸም ደረጃዎችን የማያሟሉ ሰራተኞችን የሚመለከቱ የማስተካከያ ጣልቃገብነት እርምጃ ፕሮቶኮሎችን ለማዘጋጀት MCPS ከእያንዳንዱ የሰራተኛ ማህበር ጋር አብሮ መስራት አለበት።

a) የአፈጻጸም ማሻሻያ ሂደቶች የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡ በበርካታ የመረጃ ነጥቦች ላይ በመመስረት እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ እና በተቻለ መጠን ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ እና ከስራ ጋር ተያያዥነት ያለው ከሚጠበቀው በታች የሆነ አፈፃፀምን ለማሻሻል ስልቶችን መቀየስ።

b) ከሚጠበቀው በታች ለሆነ አፈጻጸም መፍትሄ ለመስጠት ወይም ወደ ደጋፊ አገልግሎቶች ለማስተላለፍ የአፈጻጸም ማሻሻያ እቅዶች፣ እንደ አስፈላጊነቱ፣ የአቻ እገዛ እና ግምገማን ሊያካትቱ ይችላሉ። አማራጮቹ ቴክኒካዊ እውቀትን ለማሻሻል የተቀናጀ ድጋፍን ወይም ሰራተኛን በሥራ ላይ ለማቆየት፣ ለማሰልጠን ወይም ለመመደብ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ግምት ውስጥ ማስገባትን ሊያካትቱ ይችላሉ።

4. የሰራተኞችን ደህንነት ለመደገፍ እና በስራ ቦታ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን ለመፍታት ሚስጥራዊ እና በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሰራተኞች እገዛ ፕሮግራም/Employee Assistance Program መኖር አለበት።

## D. የሚጠበቁ ውጤቶች

1. MCPS ከፍተኛ ብቃት ያላቸው እና እጅግ በጣም ጥሩ የሙያ ብቃት ያላቸው የሰው ሃይል መሳብ፣ መቅጠር፣ማዳበር እና ማቆየት አለበት፣ ይህም የሚከተሉትን የሚያሟሉ ሰራተኞችን ያካተተ መሆን አለበት –

a) MCPS ለልህቀት፣ ለፍትሀዊነት፣ እና አድልዎ የሌለበት አሠራር ለሚያሳየው ቀጣይነት ላለው ቁርጠኝነት ተምሳሌት የሚሆኑ፤

b) ለሁሉም ተማሪዎች፣ ለባልደረቦቻቸው፣ እና ለሚያገለግሉት ማህበረሰብ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ማስተናገድን፣ ታማኝነትን እና አክብሮትን የሚያሳዩ እና የሚለማመዱ፤ እና

c) MCPS ውስጥ በሁሉም የስራ መደቦች ላይ ያሉ ሰራተኞች፣ ከተማሪዎች ጋር ያላቸው ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ የዕለት ተዕለት ግንኙነት፣ የስራ ልምድ፣ አንድ የሚያደርጓቸው ጉዳዮች ወይም ልዩነቶቻቸው ምንም ይሁን ምን፣ ሁሉም ተማሪዎች በእውቀት እንዲበለጽጉ የማዘጋጀት የጋራ ተልዕኮ እንደሚጋሩ እና ለዚያም ተልዕኮ አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ በየጊዜው የሚያረጋግጡ።

2. MCPS ብቃቱ እና የአመራር አቅሙ በቀጣይነት እና ወጥ በሆነ መልኩ በሚበረታታ እና በሚደገፍ እጅግ ጥሩ በሆነ የሰው ሃይል አማካኝነት አዳዲስ ሀሳቦችን/ዘዴዎችን በመጠቀም ለውጥ ማምጣት፣ በትብብር መስራት፣ እና የፈጠራ ችሎታን እና ድርጅታዊ ጽናትን ማሳየት አለበት።

## E. ክለሳ እና ሪፖርት

ይህ ፖሊሲ የሚገመገመው በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት ነው።

*ተዛማጅ ምንጮች፡-* ANN CODE ED 6-202-6-203, የሜሪላንድ ህጎች ኮድ/Code of Maryland Regulations 13A.07.06 and .08

*የፖሊሲው ታሪክ፡-* ሜይ 10, 2005 በውሳኔ ቁጥር 248-05 ጸደቀ፣የተሻሻለው በውሳኔ ቁጥር _።

~~**ጉዳዩ**~~

~~ራሱን በሚያደስ ድርጅት ውስጥ ያለ አዎንታዊ የስራ አካባቢ/ድባብ የሁሉንም ሰራተኞች ስኬት ለመደገፍ እና ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ስኬት ሁሉም ሰራተኞች ለሚያበረክቱት አስተዋፅኦ እውቅና የሚሰጡ ስርዓቶች ያስፈልጉታል።~~

~~**አቋም**~~

~~ከፍተኛ የአፈጻጸም ብቃት ያላቸው ሠራተኞችን ለመሳብ፣ ለመቅጠር፣ ለማሰልጠን/ለመምራት፣ ለማዳበር፣ እውቅና ለመስጠት እና በሥራ ላይ ለማቆየት፣ በሚጠበቅባቸው የአፈፃፀም ደረጃዎች ላይ በመመስረት ሰራተኞችን ለመገምገም፣ እና የአቻ አገዛ እና ግምገማ ለማድረግ ውጤታማ የአሠራር ስርዓቶች መኖር አለባቸው። የትምህርት ስርዓቱ ለሁሉም ሰራተኞች በፍትሃዊነት ማስተናገድን፣ በአውነተኛነት፣ በግልጽነት፣ በታማኝነት እና በመከባበር ላይ የተመሰረተ የሙያ እድገት ስርዓቶችን ይደግፋል። በተጨማሪም የትምህርት ስርዓቱ ቀጣይነት ያለው ሙያዊ እድገትን ከፍተኛ ጥራት ላለው፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን ለጠበቀ የትምህርት ስርዓት አስፈላጊ አካል አድርጎ የሚቆጥር አወንታዊ የስራ አካባቢን ይደግፋል። ስለዚህ፣ የትምህርት ሥርዓቱ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል፦~~

~~1. ስለ አንድ የስራ መደብ ሀላፊነቶች፣ ስለሚጠበቅበ(ባ)ት ሚናዎች፣ እና ጥቅማ ጥቅሞች የማወቅ እድሎችን በመስጠት ሰራተኞችን መሳብ~~

~~2. የማህበረሰቦችንን ብዝሃነት የሚያንፀባርቅ ከፍተኛ ብቃት ያለው የሰው ሃይል አጩዎችን መፈለግ እና ለተወሰኑ የስራ መደቦች እንዲያመለክቱ ማበረታታት እና ማደፋፈር~~

~~3. በግምገማ ሥርዓቱ የአፈጻጸም ደረጃዎች በሚለካው መሠረት፣ ሠራተኞቹን በሥራ ዘመናቸው ሁሉ የግለሰቦችን ፍላጎቶች በሚያሟሉ የኮሌጅ ድጋፍ ሥርዓቶች አማካኝነት ስኬታቸው እንዲጎለብት መምከር/መምራት~~

~~4. በተቀመጡት ደረጃዎች መሰረት ስኬታማ አፈጻጸምን የሚደግፉ እውቀትን፣ ክህሎቶችን፣ ችሎታዎችን፣ ልምዶችን፣ እና አስተሳሰቦችን ለማሳደግ እና ለማሻሻል በተለያዩ ልምዶች ሰራተኞችን ማሳደግ~~

~~5. ሰራተኞችን በተቀመጡ የስራ አፈጻጸም ደረጃዎች መሰረት መገምገም እና ግብረመልስ እና ሙያዊ እድገትን መስጠት~~

~~6. ለትብብር እና ለአመራር እድሎችን የሚሰጥ እና ለእያንዳንዱ ተማሪ በልህቀት ስኬትን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ የሆነ በሙያ የተካነ/ፕሮፌሽናል የትምህርት ማህበረሰብ በመፍጠር መሪዎችን መሳብ~~

~~7. የተማሪዎችን ውጤት ለማሳደግ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመደገፍ እና ለማሻሻል ጊዜያቸውን፣ ክህሎታቸውን እና ጉልበታቸውን መስዋዕት ለሚያደርጉ ሰራተኞች እውቅና መስጠት~~

~~8. ስኬቶቻቸውን የሚደግፉ የሙያ እድገት ስርዓቶችን በማዘርጋት፣ ተወዳዳሪ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅሞችን እየሰጡ ክህሎቶችን፣ ዕውቀትን፣ ልምዶችን፣ እና ችሎታዎችን የማሻሻል እድሎችን በመስጠት ከፍተኛ የአፈፃፀም ብቃት ያላቸውን ሰራተኞች በሥራ የሚቆዩበትን ሁኔታ መፍጠር~~

~~9. ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ ሊሆኑ ይችላሉ እና ሁሉም ሰራተኞች ከራሳቸው እና ከተማሪዎች አፈጻጸም በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቁ ውጤቶች አሏቸው እና አነዚህንም የሚጠበቁ ውጤቶችን ያስተላልፋሉ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሻሻል በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ተማሪዎችን መደገፍ እና እርስ በእርስ መደጋገፍ፣የተማሪዎችን ትብብር እና ውጤት ለማሳደግ መስራት የሚለውን መሠረተ እምነት የሚያሳዩ የሰራተኞችን አመለካከቶች ማሳደግ እና መደገፍ~~

~~10. የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማሻሻል የመማር ማስተማር ሂደቱን በሚደግፍ ራሱን በሚያደስ ድርጅት ውስጥ አዎንታዊ የስራ አካባቢን/ድባብን ለማሳደግ ከ MCPS የሰራተኛ ማህበራት ጋር በትብብር የመሥራት ባህል መገንባት~~

~~11. ከ MCPS የሰራተኛ ማህበራት ጋር በመተባበር የሰራተኞችን ውጤታማነት የሚደግፉ እና የሚያሻሽሉ ስርዓቶችን ማስቀጠል~~

~~12. በከፍተኛ የስነምግባር ደረጃዎች ላይ የተመሰረተ የትምህርት ስርዓትን ማዳበር/ማሳደግ እና መደገፍ~~

~~13. የሰራተኞችን ደህንነት ለመደገፍ የሚረዱ የሰራተኞች አገዛ ፕሮግራም ማዘጋጀት~~

~~14. ከፍ ያለ/የላቀ የተማሪዎችን ውጤት ለመደገፍ እና ለማበረታታት ውጤታማ፣ ቀልጣፋ በሆነ መንገድ የሰው ሀይል መመደብ~~

~~8. **ውጤቱ**~~

~~ከፍተኛ ብቃት ያለው የሰው ሀይል እና ራሱን የሚያደስ ድርጅት ማለት አዎንታዊ፣ ትብብር የሠፈነበት የስራ አካባቢ/ድባብ፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ ባሉ በሁሉም የስራ መደቦች ላይ በመማር ማስተማር፣እና በትምህርት ቤቶች~~

~~የአሰራር ስርዓት ውስጥ ወደ ልህቀት የሚመሩ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ሰራተኞች ያሉበት ማለት ነው።~~